# ጸሎትና ምስጋና

የፊልጵስዩስ መልእክት ጥናት

*ሁልጊዜ በጸሎቴ ሁሉ ስለ እናንተ ሁሉ በደስታ እየጸለይሁ፥ ከፊተኛው ቀን እስከ ዛሬ ድረስ ወንጌልን በመስበክ አብራችሁ ስለ ሠራችሁ፥ ባሰብኋችሁ ጊዜ ሁሉ አምላኬን አመሰግናለሁ። ፊል. 1፥3-5*

የምናስባቸው ሰዎች፥ ቦታዎች፥ ጊዜዎች፥ ሁኔታዎች የሚያመጡብን መልካም ወይም መልካም ያልሆነ ትዝታና ትውስታ አለ። ያደግንበትን ሠፈር ስናስብና ታስረን የተፈታንበትን እስር ቤት ስናስብ ተመሳሳይ ስሜት አይኖረንም። ታምመን በአልጋ የተቆራኘንበትን ጊዜና ተምረን የተመረቅንበትን ጊዜ ስናስብ እኩል ደስታ አይሰማንም። አንድን ሰው ለአፍታ እንኳ ስናስብ ልባችን የሚፈነጥዘውን ያህል ሌላን ሰው ስናስብ ብንውልም ንቅንቅ አይልም።

ከ20 ዓመታት በፊት ምንጃር ውስጥ የምትገኝ አረርቲ የምትባል ትንሽ ከተማ ለወንጌል አገልግሎት ሄጄ ሳለሁ ከአገልግሎት በኋላ እራት በልተን ወደ ማረፊያዬ ስንመለስ እኔና አንድ እዚያችው ከተማ የሚኖር የቤተ ክርስቲያናችን ወንድም ያልተጠበቀ ድብደባ ተቀብለን እርሱ ጎኑን እኔ ደግሞ ለሳምንት ምግብ ማኘክ እስከማልችል መንጋጭላዬ ክፉኛ ተጎድቶ ነበር። አሁን ያንን ጊዜና አረርቲን ሳስብ ቅን የሆኑ ጌታን የሚወዱ፥ ለማደግ የሚተጉ ወገኖች ይታዩኛል፤ ቡጢዋና ምግብ ማኘክ አለመቻሌም አብራ ትታሰበኛለች። አንዳንዴ ምንጃርን ሳስብ ከወገኖች አስቀድሞ የሚታወሰኝ እንዲያውም ያ የደበደበን ሰውና ያ በትር ነው።

ሐዋርያው ጳውሎስ በፊልጵስዩስ ከተማ ሲሰነብት ያሳለፈው ገጠመኝ ምን ይመስል እንደነበር በፊልጵስዩስ መልእክት ዳራ ውስጥ ተመልክተናል። ያ በእርሱ የደረሰው በብዙዎቻችን የደረሰ ቢሆን ጥሩ ትዝታ አይሆንልንም። ጳውሎስ ከሲላስ ጋር ተደብድቦአል፥ ተገፍፎአል፥ ወደ ወኅኒ ተጥሎአል። ይህ ሁሉ ደግሞ ፍትሕ በጎደለው ሁኔታ ነው የደረሰባቸው። ይህ ሁሉ ሆኖ ግን ስለ መንገላታቱና ስለ መደብደቡ፥ ስለ መከራውና ስለ እስራቱ አልጻፈም። ጳውሎስ ስለነዚህ መከራዎች ምንም ምሬት እንደሌለበት በመልእክቱ ውስጥ በጉልህ ይታያል። እንዲያውም በምሬት ፈንታ ደስታ ነው ልቡን የሞላው።

## የደስታ ጸሎት

'ሁልጊዜ ስለ እናንተ ሁሉ በደስታ እየጸለይሁ' አለ። ይህ መልእክት በአንዳንድ የመጽሐፍ ቅዱስ አስተማሪዎች 'የደስታ መልእክት' ተሰኝቶ እስኪጠራ ድረስ ደስታ በገጾቹ የተቀቡበት መልእክት ነው። ደስ እና ደስታ የሚሉት ቃላት በዚህ ደብዳቤ ውስጥ 18 ጊዜ ተጽፎ ይገኛል። በመልእክቱ ውስጥ ከተጠቀሱት ሌሎች ጭብጦች በዝቶ የተጠቀሰው ይህ ስለሆነ ነው ይህ መልእክት 'የደስታ ደብዳቤ' ሊባል የቻለው። የደስታ ምንጭ መሆን ውብ ነገር ነው። የፊልጵስዩስ ምእመናን ለጳውሎስ በእስር ቤቱ ውስጥ (ይህ መልእክት ከሁለቱ የመጨረሻ መልእክቶች አንዱና ከእስር ቤት የተላከ መሆኑን አንዘንጋ) ደስታን የሚቀዳባቸው የደስታ እንስራዎቹ ናቸው። አሁን በወኅኒ ውስጥ ሆኖ እንደልቡ መዘዋወርና ሄዶ መጎብኘት ባይችልም ሊያደርግላቸው የሚችላቸውን ሁለት ትልልቅ ነገሮች እያደረገ ነበር። እነዚህ ሁለት ነገሮች መጸለይና ደብዳቤ መጻፍ ናቸው። ሲጸልይ በደስታ ይጸልይላቸው ነበር። እጅግ ግሩም ነገር ነው።

የጥሩ ትዝታና ትውስታ፥ የምስጋናና የደስታ ምክንያትና ምንጭ መሆን እንዴት ድንቅ ነገር ነው! ባሰብናቸውና በጸለይንላቸው ቁጥር የደስታና የምስጋና ምክንያት የሚሆኑን ሰዎች አሉ? በእርግጥ ይኖራሉ። አዲስ አማኞች ሳለን የመገቡን፥ አዝነን ያጽናኑን፥ ተቸግረን የደረሱልን፥ ልክ ማቴ. 25 ውስጥ እንደተጻፈው ተርበን ያበሉን፥ ተጠምተን ያጠጡን፥ ቤት አጥተን ያስጠጉንና የተቀበሉን፥ ታርዘን ያለበሱን፥ ታመንና ታስረን የጎበኙን፥ እንዲያው ትውስ ሲሉንና ሆን ብለንም ስናስባቸው ልባችን ደ...ስስስስ እያለው የሚቆይ ሰዎች ይኖሩናል። ስለነዚህ ሰዎች ስንጸልይ ጸሎትና ደስታ አብረው ይለወሳሉ። እንዲህ ያሉ ሰዎችን በሕይወት ውስጥ ማግኘት እንዴት መታደል ነው!

በአንጻሩ ራሳችንንም በዚሁ ሚዛን እንመዝን። ሌሎች ሰዎች እኛን ሲያስቡንና ስለ እኛ ሲጸልዩ የሚሰማቸው ስሜት ምን ይሆን? እኛን ሲያስቡ ደስታ እንሆንላቸዋለን? ስለኛ ሲጸልዩስ በደስታ ይጸልያሉ? ስንታሰብና ሲጸለይልን ደስታ የሚዘገንብን ሰዎች እግዚአብሔር ያድርገን። የፊልጵስዩስ ምእመናን እንዲህ ነበሩ።

## የማያቋርጥ ምስጋና

ሐዋርያው ጳውሎስ የፊልጵስዩስን ምእመናን ባሰባቸው ጊዜ ሁሉ እግዚአብሔርን የሚያመሰግንበት ምክንያት ወንጌልን በመስበክ አብረው መሥራታቸው ነው። 'ከፊተኛው ቀን እስከ ዛሬ ድረስ ወንጌልን በመስበክ አብራችሁ ስለሠራችሁ' የሚለው ቃል ወንጌልን ከእርሱ ጋር ተጠምደው ወይም ከእርሱ ጋር ተባብረው መሥራታቸውን አይደለም። ቢሆን ኖሮ 'አብራችሁኝ ስለሠራችሁ' ይል ነበር። ይህንን ከእርሱ ጋር መተባበር በምዕራፍ 4 ያነሣዋል። እዚህ ግን ለወንጌል ሥራ እራሳቸው በራሳቸው ያላቸውን ኅብረት መናገሩ ነው። የፊልጵስዩስ ምእመናን ለወንጌል ሥራ አንድ ልብና አንድ አሳብ ነበራቸው።

የወንጌል ሥራ ከቤተ ክርስቲያን አዕማድ ተግባራት አንዱ ነው። የጤናማ ቤተ ክርስቲያን ምልክትና በጤንነት ለመቆየትዋም ዓይነተኛ ምክንያት የሆነ ኃላፊነት ነው። ወንጌልን ያለመስበክ፥ ለጠፉትና ላልዳኑ ግድ ያለመሰኘትና ያለመዘርጋት የሚታይባት ቤተ ክርስቲያን በሽተኛ ቤተ ክርስቲያን ናት። በዚህ ስትለካ የፊልጵስዩስ ቤተ ክርስቲያን ጤናማ ብቻ ሳትሆን ጉልበታምም ናት።

የወንጌል ሥራ ማለት የምሥራቹን የመናገር፥ ሰዎች ሁሉ ከክርስቶስ ውጪ የጠፉ፥ በክርስቶስ ሲሆኑ ደግሞ የሞላና የተትረፈረፈ የተባለ የዘላለም ሕይወት እንዳላቸው የማብሰር ኃላፊነት ነው። የፊልጵስዩስ ምእመናን ይህንን የወንጌል ማዳረስ ከፊተኛው ቀን፥ ማለትም፥ ጳውሎስ በፊልጵስዩስ ወንጌልን ከሰበከባቸውና እነ ልድያ ከዳኑባቸው፥ ከወንዝ አጠገብ ስብከት፥ ከልድያ ቤትና ከምኩራብ መሰብሰብ ጊዜ ጀምሮ ጳውሎስ 'እስከ ዛሬ' እስከሚለው ይህን መልእክት እስከሚጽፍበት ጊዜ ድረስ ትኩስነቱ ያልበረደ የወንጌል ሰባኪዎች ናቸው። በዚህ አገልግሎታቸው ምክንያት ባሰባቸው ጊዜ ሁሉ ስለ እነርሱ ያመሰግናል።

ስናስባቸው የደስታ ጸሎት የምንጸልይላቸውና የማያቋርጥ ምስጋና የምናመሰግንባቸው ወገኖች አሉን? እኛንስ ሌሎች ሲያስቡን እየተደሰቱ የሚጸልዩልንና አመስግነው የማይጠግቡብን ሰዎች ነን? ካሉንም ከሆንንም የተባረክን ነን። እንዲህ ያሉ ሰዎች ካልኖሩን እንዲኖሩን፥ ካልሆንንም እንዲያደርገን እንመኝ፥ እንጸልይ፥ እንጣር።

እግዚአብሔር ከአርያም ይባርካችሁ።

© ዕዝራ የስነ ጽሑፍ አገልግሎት / ዘመ

**የአሮንም ልጆች ናዳብና አብዩድ በየራሳቸው ጥናውን ወስደው እሳት አደረጉበት፥ በላዩም ዕጣን አኖሩበት፥ በእግዚአብሔርም ፊት እርሱ ያላዘዛቸውን ሌላ እሳት አቀረቡ። እሳትም ከእግዚአብሔር ፊት ወጥቶ በላቸው፥ በእግዚአብሔርም ፊት ሞቱ። ዘሌ. ፲፥፩-፪**

**በእግዚአብሔርም ፊት ሌላ እሳት ባቀረቡ ጊዜ ናዳብና አብዩድ ሞቱ። ዘኁ. ፳፮፥፷፩**




መንፈሳዊ ግለትና ትኩስነት በክርስቲያን ሕይወት ውስጥ መጠበቅ ያለበትና መብረድ የሌለበት ነገር ነው። ይህ ትኩስነትና አዲስነት በመንፈሳዊ ልደት ተጀምሮ በመንፈሳዊ ዕድገት የሚቀጥል ነው። መሆን ያለበት እንዲህ ነው። በመለኮታዊ አሠራር ይጀምራል፤ በመለኮታዊ ኃይል ይቀጥላል። የኃይሉ ምንጭ መለኮታዊ ነውና ተቀባዩ ካልታከተ ሰጪው አይነጥፍም። ተቀባዩ ደግሞ እስከ ፍጻሜው እንዲተጋ እንጂ ዳተኛ እንዳይሆን ቃሉ እንዲህ ሲል ያበረታታል፤ *በእምነትና በትዕግሥትም የተሰፋውን ቃል የሚወርሱትን እንድትመስሉ እንጂ ዳተኞች እንዳትሆኑ፥ ተስፋ እስኪሞላ ድረስ እያንዳንዳችሁ ያን ትጋት እስከ መጨረሻ እንድታሳዩ እንመኛለን፤* ዕብ. 6፥11-12

በብሉይ ኪዳን በመጀመሪያ በመሠዊያው የነደደው እሳት እንዳይጠፋ ተነግሮአል። ይህ የማያቋርጥ መስዋእት የማያቋርጥ ግንኙነትና የሰመረ አንድነት አመልካች ነው። ዘሌ. 9፥24 የመጀመሪያው እሳት ምንጭ እግዚአብሔር መሆኑን ይነግረናል፤ እንዲህ ሲል፥ *እሳትም ከእግዚአብሔር ዘንድ ወጣ፥ በመሠዊያውም ላይ የሚቃጠለውን መሥዋዕት ስቡንም በላ ሕዝቡም ሁሉ አይተው እልል አሉ፥ በግምባራቸውም ወደቁ።*

ዘሌ. 6፥12-13 ደግሞ ይህ እሳት አንዴ ከወደቀ በኋላ መጥፋት የሌለበት መሆኑን እንዲ ያስረዳል፥ *እሳቱም በመሠዊያው ላይ ዘወትር ይነድዳል፥ አይጠፋም ካህኑም ማለዳ ማለዳ እንጨት ያቃጥልበታል የሚቃጠለውንም መሥዋዕት በዚያ ላይ ይረበርባል በዚያም የደኅንነትን መሥዋዕት ስብ ያቃጥላል። ዘወትር በመሠዊያው ላይ እሳት ይነድዳል አይጠፋም።*

የክርስትና ሕይወትም መሆን ያለበት ይህ ነው። በአዲስ ኪዳን ክርስቲያንና ቤተ ክርስቲያን ከሌሎች ተምሳሌቶች ጋር በመብራትና በመቅረዝም ተመስለዋል። መብራት እንጂ መጥፋት የሌለባቸው፥ መንደድ እንጂ መክሰም የሌለባቸው ናቸው። ይሁን እንጂ ሁሌም እንዲህ አይሆንም።

የአንዳንድ ክርስቲያኖች የቀደመ ፍቅርና ግለት በተለያዩ ድካሞች ወደ መቀዝቀዝ ይወርዳሉ። ልክ እንደ ኤፌሶን ቤተ ክርስቲያን ምእመናን። ራእ. 2፥4 እንዲህ ይላል፥ *ዳሩ ግን የምነቅፍብህ ነገር አለኝ <u>የቀደመውን</u> ፍቅርህን ትተሃልና።* ለዚህ ችግር ጌታ የሰጠው የመፍትሔ ርምጃ በቁጥር 5 እንዲህ ተጽፎአል፥ *ከወዴት እንደ ወደቅህ አስብ ንስሐም ግባ የቀደመውንም ሥራህን አድርግ፤ አለዚያ እመጣብሃለሁ ንስሐም ባትገባ መቅረዝህን ከስፍራው እወስዳለሁ።* ሦስቱ መደረግ ያለባቸው ነገሮች የወደቁበትን ስፍራ ማወቅ፥ ንስሐ መግባት፥ እና የመጀመሪያውን የተተወ ነገር ማድረግ ናቸው። ይህ ካልሆነ ማስጠንቀቂያው የመቅረዙ ከስፍራው መወሰድ ነው። ምናልባት ጭል ጭል አያለ ያለ መብራት ለወዲያኛው መጥፋቱ ነው። መንፈሳዊ እሳት መክሰም የለበትም። የጌታ ተከታይ ሆኖ ሳለ የክርስቲያን ሕይወት መደብዘዝ የለበትም።

በአንጻሩ ደግሞ ሰው ሠራሽ እሳት መለኮስና መቀጣጠልም የለበትም። ሰው ሠራሽ እሳት የሚመስል እንጂ መንፈሳዊነትና መንፈሳዊ ጉልበት የሌለው፥ በስሜትና በስሜታዊነት የተሸፈነ፥ በሰዎች አነሣሽነትና ገፋፊነት ወይም ለመምሰል ሲባል የሚደረግ ሞቅታና ግለት ነው። ጉልበት ብቻ ሳይሆን ዘላቂነትም የለበትም። ስለዚህ እንደ ፋሽን በሚለዋወጡ ነገሮች፥ ክስተቶችና ልምምዶች የሚደገፍ ነው። እነዚህ ልምምዶች መንፈሳዊ የሚመስሉበት ምክንያት ምናልባት በቤተ ክርስቲያን ወይም በክርስቲያኖች አካባቢ ስለሚደረጉ ወይም ጀማሪውና አለማማጁ ክርስቲያን አገልጋይ ስለሆነ ይመስላል።

ከላይ በመግቢያው ላይ በተጠቀሱት ጥቅሶች ያልታዘዙትን ሌላ እሳት ያቀረቡት የአሮን ልጆች ናቸው። አሮንና ልጆቹ የክህነት ፈንታ የተሰጣቸው በመሆናቸው ናዳብና አብዩድ ካህናት ናቸው። ካህንነታቸው ግን የራሳቸውን እሳት የእግዚአብሔር እሳት አላደረገውም። እንዲያውም መቅሰፍት ሆነባቸው። ሰብዓዊና ስሜታዊ ልምምዶች ክርስትና ስለተነሡ መንፈሳዊ ይሆናሉ ማለት አይደለም። (ክርስትና መነሣት - በ40 ወይም በ80 ቀን - ክርስቲያን እንደማያደርግ ሁሉ ማለት ነው። ክርስትና ከክርስቶስ ጋር የመገናኘት ጉዳይ እንጂ የሃይማኖት ሥርዓት የመፈጸም ነገር አይደለም።) እንግዲህ እነዚህን ሰው ሠራሽ እሳቶች፥ መንፈሳዊ የሚመስሉ ግን ያልሆኑ ልምምዶች መፈተሻችን ምን መሆን አለበት?

እነዚህን በየጊዜው የሚፈለፈሉ አዳዲስና አሮጌ ልምምዶችን በየዋኅነትና በቀላሉ የሚቀበሉና የሚያራምዱ ሰዎች መለኪያቸው ኅሊናዊ ዳኝነት ነው። ኅሊናዊ (subjective) ዳኝነት ሲባል የአንድ ነገር ትክክለኛ መሆን ወይም ያለመሆን ነባራዊ (objective) በሆነ መለኪያ ሳይሆን በሰዎች ስሜት፣ በሰብዓዊ ልምምድ፥ በሚፈጥረው አርኪነትና ጥቅም የተደገፈ ነው። ነባራዊ በሆነው የማይለወጥ ቃል ብቻ ሳይሆን በአመክኖአዊነትም (logicality) አይደገፍም። ስለዚህ የኅሊናዊነት ስሕተት ከሰው ወደ ሰው ብቻ ሳይሆን ከጊዜ ወደ ጊዜም የሚለያይ ሚዛናዊ ያልሆነ ዳኝነቱ ነው። ለክርስቲያን የምንም ልምምድ፥ ትምህርትና ድርጊት ነባራዊ መለኪያ ቃሉ ወይም መጽሐፍ ቅዱስ ነው።

ምንም ልምምድ በቃሉ ተፈትሾ የማያልፍ ከሆነ እንድንቀበል መገደድ የለብንም። አንድ ሰው የነዚህን ልምምዶች ወይም ትምህርቶች ትክክለኛነት ቢጠረጥር ወይም ቢጠይቅ ደግሞ እንደ ስሕተተኛ ወይም ከሐዲ መቆጠር የለበትም። ከቃሉ ጋር የሚጋጭ ልምምድ በትዝብት መታየት ብቻ ሳይሆን መገለጥና ከሽፋኑ በታች ያለው ምንነት ወይም ማንነት መታየት አለበት። በእውነቱ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሚታዩ ክስተቶችና ልምምዶች ብቻ ሳይሆኑ ማናቸውም ነገሮች በቃሉ ቢመረመሩ ይህ ምርመራ መበረታታት አለበት እንጂ መወገዝ የለበትም።

ሰው ሠራሽ እሳቶች ወይም ሰብዓውያን ልምምዶች ሰው ሠራሽ ስለሆኑ ዕድሜና ጉልበት የላቸውምና ከጥቂት ወራትና ዓመታት መሰንበትና መክረም አልፈው አይሄዱም። አልፈው ሄደውም አያውቁም። አንዳንዶቹ በተጀመሩበት አካባቢ ሲከስሙ በሌላ ቀበሌ ደግሞ ይለኮሱና እዚያ ወረታቸው እስኪያልቅ ድረስ ይሰነብታሉ። በዘመናዊው ካሪዝማዊ እንቅስቃሴ ውስጥ manifestation እየተባሉ የሚጠሩ ልምምዶች የዚህ ሁነኛ ምሳሌዎች ናቸው። Manifestation ለሚለው ቃል የአማርኛ አቻ ስላላገኘሁለት ነው እንዳለ የተጠቀምኩት። ቃሉ በዐይን የሚታዩ፥ በጆሮ የሚደመጡና በሰውነት የሚገለጡ ወይም አካላዊ በሆነ ሁኔታ የሚደረጉ ትዕይንቶችን ምንነት የሚገልጥ ነው።

እነዚህ ትዕይንቶች በአንድ ቦታ በአንድ ወይም ጥቂት ሰዎች ተከስተው የሚያልፉ ልምምዶች ሳይሆኑ የሚሰነብቱና የሚከርሙ እንዲሁም በርካታ አማኞችን የሚነኩ ናቸው። ከቅርብ ዓመታት ወዲህ እየመጡ ከሄዱትና ካሉትም መካከል ጥቂቶቹን ልጥቀስ።

- በጉባኤ ውስጥ እንደ አራዊትና እንደ እንስሳት መጮኽ። እንዲህ የሚያደርጉት ነገሩን መንፈሳዊ ሲያስመስሉት እንደ ውሻ ከጮኹ አውሬ ማባረራቸው፥ እንደ አንበሳ ካገሱ ጠላትን ማስደንገጣቸው እንደሆነ ይነገርላቸዋል። ዱሮ እንዲህ የሚያደርጉ ተወስደው ይጸለይላቸው ነበር። አሁን እንደ ጤናማ ይታያሉ። ይልቅስ የነሱን ጤንነትና መንፈሳዊነት የሚጠይቁት አጋንንት እንዳለባቸው ይጠረጠራሉ። ይደንቃል።

- ማማጥ። ይህ በ90ዎቹ መጨረሻ ከቶሮንቶው ንቅናቄ በኋላ የተጀመረ ትእይንት ነው። በዚህ ልምምድ ሰዎች (ወንዶችንም ጨምሮ) ወገባቸውን ይዘው ተንበርክከው ወይም ተጋድመው ልክ ነፍሰ ጡር ሴት ልትወልድ እንደምታምጥ በመጮኽ፥ በማቃሰት፥ በመወራጨት፥ በወሊድ ሂደት ውስጥ ያልፋሉ። ይህን የሚያስደርጉ ሰባኪዎችም እነዚያ ሰዎች አንዳች መንፈሳዊ ነገር ወይም ሰው እየወለዱ እንደሆኑ ያስረዳሉ። የምንም ነገር የልደት ወረቀት ወይም የመውለዳቸው ማረጋገጫ ተሰጥቶአቸው ግን አያውቅም።

- ቅዱስ ሳቅ። ይህ ያለ ማቋረጥ እየተንከተከቱ ለረጅም ጊዜ መሳቅ ነው። ስብከት መሃልም ሊሆን ይችላል፤ ለሳቁ ሲባል ስብከቱ ቢቋረጥም ምንም እንዳልሆነ ይቆጠራል። ይህ ልምምድ አንድ ወቅት የዘመኑ የካሪዝማዊነት ፋሽን ሆኖ በብዙዎች ዘንድ እየተሰበሰቡ ጥርስ የማስጣት ነገር ሆኖ ከረመ።

- መገንደስ። ይህ ከሌሎቹ ቆየት ያለና አሁን ቀነስ ቢልም ጥቂት ባልሆኑ ካሪዝማውያን የሚደረግ ልምምድ ነው። ወደ ፊት የተጠሩ ወይም ሊጸለይላቸው የመጡ ሰዎች በትንፋሽ፥ በጣት፥ በልብስ፥ በመዳፍ እየተነኩ ወይም በጣት ማመልከት ወዘተ እንደ ዛፍ ይገነደሳሉ። ከአወዳደቃቸው የተነሣ ተደጋግመው የደረሱ አደጋዎች ስላሉ ሲወድቁ የሚደግፉና እርቃን የሚሸፍኑ አጋፋሪዎች የሚማስኑበት ልምምድ ነው።

- የማይተረጎም ልሳን። ይህ ተናጋሪው የማይተረጉመው፥ ሌላም የማይተረጉመው ምን እንደተባለ ማንም የማያውቅበትና ስለዚህም የማይታነጽበት ልሳን ብዙዎች በሚገኙበት የመናገር ልምምድ ነው። በ1ቆሮ. 12-14 ስለዚህ በግልጽ ቢጻፍም የተጻፈውን ከመታዘዝ በልምምድ መታገዝ አይሎ ሲገዛ ይታያል።

እነዚህ የውሸት ፈውሶችን፥ የማይፈጸሙ ትንቢቶችን፥ የግምትና መላ-ምት ‘መገለጦችን’ (መገለጥ የሚባል የጸጋ ስጦታ አለመኖሩን ሳንዘነጋ) ሳንነካ ነው። ከላይ የተጠቀሱትን ጥቂት ምሳሌዎች ስንመለከት ልምምዶቹ ስሜትን ሊነኩ፥ እውነት ሊመስሉ፥ በአንዳንዶች እንዲያውም የመንፈሳዊነት መስፈሪያ ተደርገው ሊቆጠሩ ይችላሉ። ግን እነዚህ ነገሮች ሰው ሠራሽ ልምምዶች ናቸው? ወይስ በቃሉ የተደገፉ ጉባኤን የሚያንጹ ድርጊቶች ብሎ መጠየቅ ትክክለኛ አካሄድ ነው። አንዳንድ የዋሆች፥ “እነዚህ ልምምዶች ተለማማጁን እስከጠቀሙ ድረስ ምንም ጉዳት የለባቸውም” የሚል አቋም አላቸው። ከነዚህ የማይርቁት ደግሞ፥ “ሌላውን እስካልጎዱ ድረስ ቢኖሩ ምንም ችግር የለበትም” የሚል አስተሳሰብ አላቸው። ለነዚህ ምንጩ ሳይሆን ውጤቱ ነው መለኪያው።

የተለማማጁ ጥቅም መለኪያ ምንድርነው? ሌላውን አለመጉዳታቸውና፥ እነርሱን ራሳቸውንም አለመጉዳታቸው የሚፈተንበት መፈተኛ አለ? ነባራዊ በሆነው የማይለወጠው መፈተሻችን በእግዚአብሔር ቃል እነዚህን ነገሮች መፈተሽ እነዚህ ነገሮች ሰማያዊ ወይም ምድራዊና ሰው ሠራሽ መሆናቸውን ለመለየት ይረዳናል። ሰው ሠራሽ ብቻ ሳይሆኑ ሰይጣን ሠራሽ እሳቶች በቤተ ክርስቲያን እልፍኝ ውስጥ እየነደዱ መሆናቸውን ላለማየት አንገታችንን ማዞር የለብንም።

የአምልኮ ወቅት ጩኸት፥ ውኃ የማያነሡ መዝሙሮችን ለማሞቅና ለመሸፈን የሚደረግ ከልክ ያለፈ የሙዚቃ መሣሪያ ድምጽ፥ ተጨምቆና ተገድዶ የሚደረግ ጭብጨባና እልልታ፥ እየተጠየቀና እየተለመነ የሚባል ‘አሜንና ሃሌሉያ’፥ የአማኞችን ስሜት ማጦዝ ወዘተ መንፈሳዊ መቀጣጠል የሚመስላቸው ጥቂቶች አይደሉም። ለነፍሳችን የሚቀርልንና ለዘመንና ለዘላለማችን የሚሆንልን ስንቅ አገኘን? ለረጅሙና ዋጋ የሚያስከፍለው ጉዞ የሚሆን ጉልበት አገኘን? ከፊት ይልቅ ለተሻለና ለላቀ ግንኙነት ታደስን? ክርስቶስን ያላወቁ ልባቸውን የሚመረምር፥ ኃጢአተኝነታቸውን የሚናገር ቃል ሰሙ? በእውነትና በመንፈስ እግዚአብሔር ተመለከ? ብለን ብንጠይቅ መልሳችን ስውር አይሆንም።

እሳት ሁሉ እሳት አይደለም። ለብ ለብ ክትፎም እሳት ሸቶታል። እመንገድ ዳር በቆሎ ጥብስ የሚሸጡልን ሰዎች የሚጠብሱት በቆሎም እሳት ነክቶታል። ብቻ ሁለቱም ከውስጥ ጥሬ ናቸው። ከ3 ዓመታት በፊት ባለቤቴ ወላጆቿን ልትጎበኝ ሄዳ ያዘጋጀችልኝም ምግብ ስላለቀ ከግሮሰሪ ሁሉ ነገር የተጨመረበትና ሊበስል የተዘጋጀ ሊጥ ፒሳ ገዝቼ መጣሁና ማብሰል ጀመርኩ። ለ15 ያህል ደቂቃ መብሰል እንዳለበት ብቻ ነው በችኮላ ያነበብኩት። ከዚያ 15 ደቂቃ ጠብቄ ሳወጣው አሁንም ሊጥ ነው። ሊጡ ግን በጣም ይሞቃል፤ እንዲያውም ያቃጥላል። እላዩ የተጨመሩት ነገሮች በስለው ተንጨርጭረዋል። ኋላ ግራ ሲገባኝ ደውዬ እርሷን አላገኘሁም ግን የሆነው ስናገር ያገኘኋት ልጅ፥ “በምንድነው ያበሰልከው?” አለችኝ። “በማይክሮዌቭ ነዋ!” አልኳት። “አይደለም፥ የሱ ዓይነት ፒሳ የሚበስለው በምድጃ (oven) ነው። ለዚያውም ምድጃው አስቀድሞ ግሎ ነው” አለችኝ። አወይ ጉድ! የኔ ፒሳ ለ15 ደቂቃ በሰው ሠራሽ የማይክሮዌቭ እሳት እስከ ውስጡ ተጠብሶአል፤ ግን አልበሰለም። ሊጥ እንደተጠፈጠፈ ገብቶ ሲወጣም ሊጥ ነው! የሞቀ ነጭ ጥሬ ሊጥ።

ሰው ሠራሽ እሳት ሊለበልብም ሊያቃጥልም ይችላል፤ ግን አያበስልም። የናዳብና የአብዩድ እሳት ሌላ እሳት ነበረ። የራሳቸው እሳት ነበረ። የሚያሳዝነው እነዚህ ሰዎች የጠፉትም በእሳት ነበረ። አገልጋዮችም ተገልጋዮችም ይህን እንጠይቅ፤ የምንቆሰቁሰው፥ የምናነድደው፥ የምናራግበው እሳት “በምድር ላይ እሳት ልጥል መጣሁ” ያለው ጌታ የለኮሰው እሳት ነው ወይስ የኛ እሳት?

ጌታ ከአርያም ይባርካችሁ። ዘ.መ.

## የመጽሐፍ ቅዱስ ጥያቄዎች

ከታች በቤተ ክርስቲያናችን በምናትማት ትንሽ መጽሔት ከምናወጣቸው ጥያቄና መልስ ውድድሮች ገጽ ውስጥ የተወሰደ ክፍል ይገኛል። ለእናንተም የመጽሐፍ ቅዱስ እውቀት ትንሽ መፈተሻ እንድትሆን ወይም አትማችሁ በቡድንና በቤተ ክርስቲያን እንድትጠቀሙበት እንዳለ በመውሰድ (ከማስታወቂያው ጋር) አትሜአለሁ። ሌሎቹንም ጥያቄዎች ለማግኘት ብትፈልጉ ጠይቁ።

የመጽሐፍ ቅዱስ ጥያቄዎች መልስ የምትሰጡ መመለሳችሁን ቀጥሉ። ከሚቀርቡት 300 ጥያቄዎች በዚህ እትም 140 ደርሰዋል። ከታች ባለው ሰንጠረዥ በ8ቱም አቅጣጫ ሠላሳ የመጽሐፍ ቅዱስ ሰዎችን ስሞች በመፈለግ ካገኛችሁ በኋላ በቀሩት ባልተሠሩባቸው ዘጠኝ ፊደሎች ጌታን በማመናችን ከምናገኛቸው ነገሮች አንዱን ጻፉ። አንዳንድ ፊደሎች ተደጋግመው ጥቅም ላይ ሊውሉ ይችላሉ።

| | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| አ | ብ | ያ | ታ | ር | ያ | ስ | ሎ | ው | ጳ |
| ብ | ብ | ቆ | ዕ | ያ | ም | ቃ | ዔ | ዘ | ዮ |
| ደ | ም | ር | ን | ላ | ህ | ሉ | ሊ | ሎ | ለ |
| ና | ኮ | ር | ሃ | ታ | ነ | ቤ | ቂ | ኖ | ቀ |
| ጎ | ል | ያ | ድ | ም | ና | ሴ | ዮ | ዮ | ስ |
| ል | ሔ | ራ | ቤ | ሩ | ት | ሞ | ለ | ሐ | ስ |
| ቤ | ሮ | ኢ | ዮ | ብ | ና | ት | ይ | ን | ና |
| አ | ቤ | የ | ኢ | ት | ኤ | ወ | ሕ | ስ | ዮ |
| ቴ | ል | ጌ | ል | ቴ | ል | ፊ | ል | ሶ | ር |
| ቲ | ቶ | ል | ያ | ት | ላ | ሰ | ዝ | ዔ | ቦ |

መልስ፦ ______________________________